# ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለግንዛቤ የሚረዳ መልዕክት (ሰርፀ ደስታ)

June 28, 2018

ወያኔ አጥፍቶ ጠፊ አሸባሪ ቡድን እንደሆነ ቀድመው ጥቂቶች ቢያውቁም ብዙዎቻችን አልገባንም ነበር፡፡ እስከዛሬ ከወያኔ መንፈስ ከተጠናወታቸው ግለሰቦች ጋር በአመክንዮ (ሎጂክ) እንግባባለን ብለው መከራ ሲያዩ የሚታዩ አሁንም ብዙዎች ናቸው፡፡ ይህ የሽብር ቡድን አገሪቱን ከወረረ ጀምሮ እስከዛሬም ሲሰራ የነበረው የጣፋት ሴራውን የሚያስኬድበትን መዋቅሮች ነበር፡፡ ወያኔ ከመምጣቷ በፊት የእኔ ብጤ መስለው የተለያየ የሥለላ ሥራ ሲሰሩ አንዳንዴም እየፈነዱም እያፈነዱም ነበር፡፡ ያኔ አቅሙ ስላልነበራቸው በጣም ተጠንቅቀው ነበር፡፡ አሁን ግን አቅም አግኝተናል በለው የትኛውንም አይነት አረመኔያዊ የመጨረሻ እድላቸውን እየተጠቀሙ ነው፡፡ ብዙ መወናበድ አያስፈልግም፡፡ የሚያስፈልገው መተባበር ግን በሳል መሆን ነው፡፡ ልብ በሉ ከወያኔዎች ወደራሳቸው የተመለሱ ግን በፍርሀት ያሉ አሉ፡፡ በግልጽ ግን እኛም የምናውቃቸው በሕዝብ ላይ በይፋ እየፎከሩ ያሉ አሉ፡፡ እነዚህን ያለምንም ቅድመሁኔታና መለሳለስ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ ብዙ የእኔ ብጤ መስለው በየሰፉሩ ያሉ አሉ፡፡ ሕዝብ እያንዳንዱን የእኔ ብጤ መስሎ የሚንቀሳቀስ አጣርቶ መፈተሽና ማወቅ አለበት፡፡ ዛሬ አሁን ላይ አነዋር መስኪድ አካባቢ እየተቃጠለ ነው፡፡ መስኪዱ በምን ሁኔታ እንዳለ አላወቅንም፡፡  ጎንደር ተመሳሳይ እሳት አለ ይባላል፡፡ አዋሳና ወልቂጤ ሰሞኑን የሆነውን አይተናል፡፡ አሁን ደግሞ አሶሳ፡፡ በባሕርዳርና ጎንደር ቦምብና የመገናኛ ሬዲዮ ያላቸው የእኔ ብጤዎች እየተያዙ ነው፡፡ በአለፈው ቦምብ ያፈነዱትንም አይተናል፡፡ ይህ በእኔ ብጤ መልክ ነው፡፡

ዋናዎቹ ግን ከላይ ሆነው የመረጃና አስፈላጊ ቁሳቁስ የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ በባለፈው የደቡቡ ብጥብጥ ሽፈራውና የደቡቡ አስተዳዳሪ ገጠር እየዞሩ ሕዝብ ሲያነሳሱ እንደነበር ተነግሯል፡፡ ዝም ብሎ የሰፈር ወሬ አይምሰላችሁ፡፡ ሰሞኑን አሶሳ አካባቢ አባይ ጸሀዬ ታየ የሚሉ አሉ፡፡ ልብ በሉ እነዚህ ሰዎች የራሳቸው ጠባቂ ያላቸው ናቸው፡፡ በረከት ስምኦን፣ ህላዌና የመሳሰሉት ሰቆጣ መሽገዋል ይባላል፡፡ የሰቆጣ ሕዝብ አልገባኝም እንዴት መደበቂያ እንደሆነ፡፡ የአሶሳውን አስመልክቶ ችግር ፈጠረ የተባው የበርታ ማሕበረሰብ ነው፡፡ ይህን ሕዝብ እኔ እንደማውቀው አጅግ የተለየ ስብዕና ያለው ሕዝብ ነው፡፡ ኑሮው ራሱ የተመሰረተው ከሌሎች ጋር አብሮ በመኖር ነው፡፡ በርታ ገጠር ውስጥ ገብታችሁ በራሳችሁ ቋንቋ ነው የሚያወሩአችሁ፡፡ አረብኛ፣ ኦሮምኛና አማርኛ ያወራሉ፡፡ ኑሮአቸው ጠረፍ አካባቢ ስለሆነም ይመስላል ዋና ሕይወታቸው የተመሰረተው ከሰዎች ጋር በአላቸው መስተጋብር ነው፡፡ የቋንቋ ችሎታቸውም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ይመስላል፡፡ የበርታ ሕዝብ እስከዛሬ ችግር ፈጠረ ሲባል ሰምቼም አላውቅም፡፡ አሁን ላይ እየሆነ ያለው ከዚህ ውጭ በሆነ በተደራጁ ኃይላት ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ በምስል ብዙ ሰዎች ዱላ ይዘው መንገድ ላይ የሚታየው የበርታ ሕዝብ ሳይሆን ከተለያየ ቦታ ሄዶ አሶሳ የሚኖረው ሕዝብ ይመስላል፡፡ ችግር ግን ተከስቷል፡፡ ወያኔና ኦነግ አሁን

ጥምረት ፈጥረው ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ አብይ ላቀረበው ጥሪ የዳውድ ኢብሳ ንግግር አንዱ ምልክት ነው፡፡

ዛሬ ሌላ አንድ ቀላል የሚመስል ግን ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነገር በአርቲስ አስቴር በdhaኔ ላይ ተፈጽሟል፡፡ ይህ ጉዳይ ቀላል ይመስላል ግን ማን ነው ይህን ያደረገ የሚለውን ችላ ማለት አሁንም ስህተትን ማስተናገድ ነው፡፡ በየቦታው ወያኔ ትግሬዎችና አጋሮቻቸው መጨረጨረሻቸው ስለሆነ የቻሉትን ሁሉ ማድረግን ቀጥለዋል፡፡ በቅዳሜው ፍንዳታ ወቅት ከተቃጠለው መኪና ሌላ የፖሊስ መኪና በሰላማዊ ሰልፉ መሀል እዝብ በአለበት እንዴት ሲነዳ እንደነበር በኋላም በሕዝብ እንደቆመ አይታችኋል፡፡በአዲስ አበባው ፖሊስ ኮሚሽነር በኩል የታዘዘው ከዚህ የከፋ ብዙ እንደሆነ እናያለን፡፡

ሌላው የቅዳሜውን ሰልፍ አስመልከቶ አልዘገባችሁም ተብለው የትግራይ ክልል ቴልቪዥንና ኢኤንኤን በብሮድካስ ባለስልጣን ማብራሪያ እንዲሰጡ ተጠይቀዋል፡፡ አንዳንዶች አጉል ፍትህዊ ለመምሰል ይሞክራሉ፡፡ ኢኤንኤን አለመዘገብ መብቱ ነው ለምን ይጠየቃል አይነት ወሬ ያዛምታሉ፡፡ የአገሬ ልጅ አትሸወድ፡፡ እንዲህ ያለ ፍትህ የለም፡፡ ጠያቂው አካልም ሥራው ይሄ ነው፡፡ ኢኤንኤንም ሆነ ትግራይ ቲቪ ምን አልባትም በእለቱ የሚሆነውን ስለሚያውቁ ራሳቸውን ከአደጋ ለማራቅ እንደሆነ አስተውሉ፡፡ ተራ የፌስ ቡክ ወሬ ይመስላል ግ አርብ ለቅዳሜ አንዳንዶች አብይ በገዛ ጠባቂው በሽጉጥ ተመታ ሲሉ ነበር፡፡ ይህ ስልት መሆኑን አትዘንጉ፡፡ የታሰበው እንደዛ እንዲመስል ነበር፡፡ ስለዚህ ቀድመው እንደዛ ያወሩልናል እኛም ጠባቂዎቹ ላይ ደምድመን ቁጭ እንድንል ነው፡፡ ይህ ታስቦበት የሆነ ነው፡፡ እንደተባለውም ወደመድረኩ የታጠቁ ሰዎች ሊገቡ ሲሉ ተከልክለው አምባጓሮም ፈጥረዋል፡፡ በፍትህና በሰበአዊነት እያሳበባችሁ ለአሸባሪዎች ከለላ የምትሰጡ ተቆጠቡ እንላለን፡፡ ስለኢኤን ኤን መጠየቅ ትክክል አደለም ሲሉ ያየኋቸው ደግሞ ዋና የወያኔ ተቃዋሚ የሚመስሉ ናቸው፡፡ ሁሉም ግን እሰከ አሁንም የአብይ ጉዳይ ቅር ይላቸዋል፡፡ እንደነ ዳንኤል ብርሀኔና አሉላ ሶሎሞን መሆን አይጠበቅም፡፡ ለወያኔ ከእነዚህ ይልቅ በቁርጥ ቀን የሚውሉላት እነዚህ ተቃዋሚ የሚመስሉት ናቸው፡፡

መደረግ ያለበት በአስቸኳይ የሸብር ቡድኑ መሪዎች በቁጥጥር ሥር መዋል አለባቸው፡፡ እነማን አትበሉኝ፡፡ አባይ ጸሀዬ፣ በረከት ምናምን እያልኩ ስዘረዝር አልውልም፡፡ የትግራይ ተወላጆች እድሉ ቀርቦላችኋል፡፡ ለጤነኞቹ ማለቴ ነው፡፡ በአለፈው አንዱ ተይዞ የሆነ ቤተክርስቲያን ዲያቆን ሆኖ ስለተገኘ ተለቀቀ የሚል ወሬ ተሰራጭቶ ነበር፡፡ አስተውሉ እንኳን ዲያቆን ጳጳስ ቢሆን በወያኔ መንፈስ የተጠመቀ አሸባሪ አደለም ማለት ጭራሽ አደገኛ የሆነውን አሸባሪ ለጥፋት መተው ነው፡፡ እንደተባለው ዲያቆን ሊሆን ይችላል ግን ዲያቆን መሆኑ ከወያኔ አሸባሪነት አያድነውም፡፡ ዛሬ እኮ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው ዋና የሽብር መሪዎቹ የተቀመጡት፡፡ ሕዝብ በፍጹም መሸወድ የለበትም፡፡ ይህ የእርግማናችን ውጤት ቢሆንም! አደገኛ ቦታዎች እንደውም ከዚህ በኋላ አብያተ ክርስትና፣ መስኪድ እና የመሳሰሉት እንደሚሆን እገምታለሁ፡፡

በአስቸኳይ ቢያንስ የተወሰኑት መያዝ ይገባቸዋል፡፡ ሕዝብ በያለበት ማንም ይሁን ማን ራሱን ከእነዚህ ፍጡሮች መጠበቅ አለበት፡፡ ትልቅ ባለስልጣን ቢሆን እነኳን አላስፈላጊ እንቅስቃሴ ሕዝብ ከአየበት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ አብይ አሁን ትኩረት አድርገን ጠላቶቻችንን በሙሉ አንድ ወር በአልሞላ ጊዜ ውስጥ በቁጥጥር ሥር ማዋል ይገባናል፡፡ ወያኔ የኢትዮጵያ የሆነውን ሁሉ አጥፍታ በራሷ የሴራ ሕግ ነው ዛሬ ሕግ የሚሉን፡፡ ሌላው ሥማቸው የተቀየረ ተቋማት በአስቸኳይ ወደነበረ ሥማቸው አስፈላጊ ሲሆን ለአገርና ሕዝብ ትልቅ አስተዋጾ በአደረጉ ሰዎች እንዲሰየሙ፡፡ ብዙ ቦታ ተመሳሳይ ነገር ሊኖር ይችላል ግን አንድ ሁሌም የሚያናድደኝ ነገር የታሪካዊው የሆለታ ገነት ጦር ት/ቤት በወንበዴ ወያኔ ሥም መቀየሩ ነው፡፡

አንድ ነገር አስተውሉ ሁሉም በወያኔ ሥም አደለም የእኛ ትኩረት፡፡ በእርግጥም እስከዛሬ ወያኔ ትግሬ ሁሉ ከወያኔ ጋር ሲያጋፍር ቢቆይም ከሆኔታዎች ጋር ራሳቸውን የቀየሩ ይኖራሉ አሉም፡፡ ከትልቁ እስከ ትንሹ ግን ወንጀላቸውና ግፋቸው ራሱ እያቅበዘበዛቸው ምህረትን ያልፈለጉት በእርግጥም ጥሩ ነው፡፡ በምህረት ሥም ፍርድ ከሚጓደልም እስከዛሬ በሰሩት ምህረት ቢደረግላቸውም አሁን በሚፈጽሙት ወንጀል ምንም አይነት እደል ሊሰጣቸው አይገባም፡፡ አሁን እያደረጉት ያለው የሽብር እንቅስቃሴ ጋንጌን ሰካላ ኩቴ ጀናን ኦፊቱ ገባብሲቴ (በቅሎ ስካሏን በጠሰች ቢለው በራሷ  አሳጠረች) እንዳለው ነው የአገሬ ሰው፡፡

በመጨረሻም የአብይ ደጋፊ በመምሰል በየዲያስፖራው ዋና የአብይ ጉዳይ አስተባባሪ እየሆኑ ያሉ አካላትን በትኩረት ማየት ጥሩ ነው፡፡ በአሜሪካማ ጭራሽ አብይን የምጠራው እኔ ነኝ እኔ ነኝ በሚል ጳብ ፈጥረዋል አሉ፡፡ በዚህ አጋጣሚ አብይ መንቀሳቀስ ያለበት በራሱ እቅድ እንጂ በዲያስፖራ ግብዣ ሊሆን እንደማይችል ላስገነዝብ አወዳለሁ፡፡ አብይ ለምንስ አሜሪካ ይሄዳል? የመሪ ፕሮቶኮል የማይገባው በወያኔ ወንበዴ ቡድን የለመደውን በአብይ ባያስብ ጥሩ ነው፡፡ የዲያስፖራው አላማ የሕዝብና አገር ጉዳይ ሳይሆን አገር ቤት በሚመጣው ለውጥ አጋጣሚ የሚጠቀምበትን ያሰላ ነው፡፡  ለማንኛውም አገርና ሕዝብ አሁን በትኩረት በጠላቶቹ ላይ በአንድነት መዝመት አለበት!

አመሰግናለሁ!

ቅዱስ እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ! አሜን!

ሰርፀ ደስታ